የወ/መ/ቁጥር 159531

የልደታ ምድብ 5 ኛ ወንጀል ችሎት

ሐምሌ 07 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኛ ውበቱ አሰፋ

ከሳሽ፣ የፌደራል ዐ/ሕግ - አቶ መሳይ ተድላ ቀረበ

ተከሳሽ፣ ወ/ሮ ሙሪዳ መርካ በሀ - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጠ።

<u>ፍርድ</u>

ዐ/ሕግ ነሐሴ 13 ቀን 2001 ዓ.ም በተሻፈ የወንጀል ክስ አቤቱታ ተከሳሽ በ 1996 ዓ.ም የወጣውን የወንጀል ሕግ አንቀፅ 615 ላይ የተደነገገውን በመተላለፍ የሌላ ሰውን ክብር ለመንካት በማሰብ ሐምሌ 16 ቀን 2001 ዓ.ም በግምት ከቀኑ 5፡00 ሰዓት ሲሆን በኮልፌ ቀራንዮ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 01/05 ልዩ ቦታው አለም ባንክ መኖር በሀገር አካባቢ የግል ተበዳይ ወ/ሮ ዙልፋ አብደላን አንቺ ኪስ አውላቂ የኪስ አውላቂ ሚስት በማለት በቀጥታ በመናገሯ በፈፀመችው ስድብና ማዋረድ ወንጀል ተከሳለች በማለት ያቀረበ ሲሆን የዐ/ሕግ የክስ አቤቱታ ለተከሳሽ ደርሷትና ተነቦላት ከተረዳችው በኋላ ክሱን ሳትቃወም፤ ድርጊቱን አልፈፀምኩም፤ ጥፋተኛ አይደለሁም ብላ ክዳ በመከራከሯ ዐ/ሕግ የግል ተበዳይን ጨምሮ ሦስት ምስክሮችን በማቅረብ ያሰማ ሲሆን ምስክሮቹም በክሱ ላይ በተመለከተው ቀን፤ ሰዓት ቦታ ተከሳሽ በክሱ ላይ የተገለፀውን የስድብና ማዋረድ ድርጊት መፈፀሟ በመረጋገጡ በወንጀል ሕግ አንቀፅ 615 ስር እንድትከላከል በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ ሥርዓት ቁጥር 142(1) መሰረት ታዛለች።

ተከሳሽም እከላከላለሁ ብላ ሁለት የመከላከያ ምስክሮችን በማቅረብ ያሰማች ሲሆን በጭብጥነትም በወቅቱ ሐምሌ 16 ቀን 2001 ዓ.ም ከቀኑ 5፡00 ሰዓት ሲሆን ወደ ቤቴ መጥተው ደክ ላይ የነበረ ፅድ ተነቅሌ አጥሩንም ተነስቶ በማየቴ ፅዴን ማን ወሰደ፤ ምን አይነት ሌባ ነው የወሰደብኝ ስል ስሚራ የተባለችው ጎረቤቴ ስሜን ጠርታ ለምን ሌባ ብለሽ ስሜን ጠርተሽ አትሰድቢኝም በማለት ስትናገረኝ አንቺን አልጠራሁሽም ማለቴን የተነጋገርኩትም ከእሷ ጋር ብቻ መሆኔን እንጅ ከተከሳሽ ጋር ያለመሆኑን አስረዳለሁ በማለት ያስመዘገበች ሲሆን የመከላከያ ምስክሮችም መጋላ ፈፅመው የመሰከሩ ሲሆን ቃላቸውም ከመዝገቡ ጋር ተያይዟል።

ፍ/ቤቱም ተከሳሽ ባቀረበችው የመከላከያ ማስረጃ በዐ/ሕግ በኩል የቀረበባትን ክስና ማስረጃ አስተባብላለች ወይ የሚለውን ነጥብ የመረመረ ሲሆን ተከሳሽ የስድብና ማዋረድ የወንጀል ድርጊቱን ፈፅማለች ተብሎ ክስ የቀረበባት ሐምሌ 16 ቀን 2001 ዓ.ም ሲሆንና የተመሰከረውም በዚሁ ቀን ሲሆን፤ የተከሳሽ ሁለት የመከላከያ ምስክሮች ግን የምስክርነት ቃላቸውን የሰጡት መስከረም 16 ቀን 2001 ዓ.ም ተፈፀመ ስለተባለ ድርጊት ነው። መስከረም 16

ቀን 2001 ዓ.ም ደግሞ ተከሳሽ የወንጀል ድርጊት ፈፀሙ ተብለው አልተከሰሱም። በመሆኑም ተከሳሽ ባቀረቡት የመከላከያ ማስረጃ በወ/ሕግ በኩል የቀረበባቸውን ክስና ማስረጃ ለማስተባባል ስላልቻሉ በወንጀል ሕግ አንቀፅ 615 ስር ጥፋተኛ ናቸው በማለት በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ ሥርዓት ቁጥር 149(1) መሰረት ውሳኔ ተሰጥቷል።

<u>የቅጣት አስተያየት</u>

<u>ዐ/ሕግ</u>፡ የምናቀርበው የቅጣት ማክበጃም ሆነ ማቅለያ የለም፤ ነገር ግን ተከሳሽ
የሕፃን እናት ስለሆኑ በሕገ መንግስቱ አንቀፅ 36(2) ላይ የተደነገገው
ከግንዛቤ ገብቶ እንዲወሰን በማለት አመለከተ።

<u>ተከሳሽ</u>፡ ዕድሜዬ 27 ዓመት ነው፤ ትዳርና ሦስት አካለመጠን ያላደረሱ የ 10 እና
7 ዓመት ልጅ እንዲሁም የ 45 ቀን ሕፃን አለኝ፤ ሥራ የለኝም፤
በባለቤቴ ገቢ ነው የምተዳደረው በማለት አመለከተች።

ፍ/ቤቱ ጉዳዩን መርምሮ የሚከተለውን ቅጣት ወስኗል።

<u>ውሳኔ</u>

በወንጀል አድራጊ ላይ የሚወሰነው ቅጣት ወንጀል ሕጉን ግብና ዓላማ በሚያሳካ መልኩ ሊሆን እንደሚገባ የታመነ ነው። በዚህም መሰረት የወንጀል ሕግ ዓላማ ለጠቅላላው ጥቅም ሲባል የአገሪቱን መንግስት፤ የነዋሪዎቿን ሰላም፤ ደህንነት፤ ሥርዓት፤ መብትና ጥቅም መጠበቅና ማረጋገጥ ነው።

የወንጀል ሕግ ግብ ደግሞ በዋናነት ስለወንጀሎችና ስለቅጣታቸው በቅድሚያ ማስጠንቀቂያ በመስጠት ወንጀል እንዳይፈፀም መከላከል ሲሆን፤ ሕጉን ተላልፈው ወንጀል የሚፈፅሙትን ደግሞ ተቀጥተው ሌሎች ወንጀል እንዳይፈፅሙ፤ እንዲቆጠቡና ለሌሎች ማስተማሪያ እንዲሆኑ ወይም እንዲታረሙ በማድረግ ወይም ተጨማሪ ወንጀሎች እንዳይፈፀሙ እርምጃዎች እንዲወሰድባቸው ማድረግ ስለመሆኑ በ 1996 ዓ.ም ከወጣው የኢ.ፌ.ዲ.ሪ.የወንጀል ሕግ አንቀፅ 1 ድንጋጌ ለመገንዘብ ይቻላል።

የወንጀል ሕጉን ግብና ዓላማ ለማሳካት ፍ/ቤቱ በወንጀለኛው ላይ የሚወስነው ቅጣት በአንድ በኩል ወጥነትን፤ ተመዛዛኝነትን እና ፍትሀዊነትን ለማረጋገጥ በሌላ በኩል ደግሞ የወንጀል አድራጊውን ግላዊ ባህሪና የወንጀል አፈፃፀም ክብደት መዝኖ ቅጣት ለመወሰን እንዲያስችል ታስቦ የወጣውን የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የወንጀል ቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 1/2002 እና የወንጀል ሕጉን ድንጋጌዎች መሰረት ተደርጎ የሚከተለው ቅጣት ተወስኗል።

ተከሳሽ አሁን ጥፋተኛ የተባለችበት በ1996 ዓ.ም የወጣው የወንጀል ሕግ 615/የስድብና ማዋረድ ወንጀል ገና ደረጃ ያልወጣለት በመሆኑ የወንጀል ደረጃ እና እርከን የሚወሰነው በቅጣት አወሳሰን መመሪያው አንቀፅ 13 መሰረት ነው። የደረጃ አወሳሰኑም ማክበጃውና ማቅለያው ታሳቢ ከመደረጉ በፊት በወንጀሉ ክብደትና አፈፃፀም መሰረት እንደሚወሰን መመሪያው በደነገገው መሰረት ደረጃው በሦስት ደረጃዎች ሀ. ዝቅተኛ፤ ለ. መካከለኛ እና ሐ. ከባድ ደረጃ በማለት ይለያል።

ፍ/ቤቱም በወንጀሉ ክብደትና አፈፃፀም መሰረት የወንጀሉን ደረጃ ለመወሰን የስድብና ማዋረድ ወንጀል አፈፃፀሙ ሲታይ ቀላል እንጅ ሌላ ከባድ የሚያስብል ነገር ባለመኖሩ ደረጃው ዝቅተኛ ተብሎ ተወስኗል።

በወጣው ደረጃ መሰረት እርከን ለመወሰን በሕጉ አንቀፅ 615 ላይ የተመለከተው ከሦስት መቶ ብር በማይበልጥ መቀጮ ወይም ከሦስት ወር በማይበልጥ እስራት ያስቀጣል። ከሁለቱ የቅጣት አይነቶች በቅድሚያ ፍ/ቤቱ አንዱን መለየት ስላለበት ከተፈፀመው የወንጀል ድርጊት አንፃር ተከሳሽን ያርማል፤ ወደፊትም ያስተምራል ብሎ ፍ/ቤቱ ባመነበት በመቀጮ እንድትቀጣ ተወስኗል።

ከዚህ በላይ በተመለከተው የቅጣት ደረጃ መሰረት ቅጣቱን ለመወሰን በቅጣት አወሳሰን መመሪያው አንቀፅ 13(10) ላይ በተመለከተው መሰረት የወንጀሉ ደረጃ ዝቅተኛ ስለሆነ የገንዘብ መቀጫው ደግሞ ከብር አስር እስከ አንድ መቶ ብር ስለሆነ በዚህ ፍቅድ ስልጣን መሰረት ከተከሳሽ የገቢ ምንጭ አንፃር ለፈፀሙት ጥፋት ያርማል ወደፊት ያስተምራል ብሎ ፍ/ቤቱ ባመነበት በብር 100.0(አንድ መቶ ብር) መቀጮ እንድትቀጣ ተወስኗል።

<u>ትዕዛዝ</u>

1 ኛ. ተከሳሽ የቅጣት ገንዘቡን ስትከፍል ትለቀቅ።

2 ኛ. በዚህ መዝገብ የተገባ የዋስትና ግዴታ ቀሪ ሆኗል።

3 ኛ. የይግባኝ መብት እንዳለ በችሎት ተነገረ።

4 ኛ. መዝገቡ ተዘጋ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ።